## ጉባኤ ቍስጥንጥንያ 381 ዓ.ም

በዚህ ጉባኤ ውስጥ ከተወሰኑት ዋና ዋናዎቹ:-

ሀ/ በምስጢረ ሥላሴ፣ መንፈስ ቅዱስን ሕጹጽ ነው ብሎ ያስተማረ የመቅዶንዮስ መወገዝ፤

ለ/ በምስጢረ ሥጋዌ፣ ቃለ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም ብሎ ያስተማረ የአቡሊናርዮስ መወገዝ፤

ሐ/ የእግዚአብሔር ልጅ የተዋሐደው የአዳምን ሥጋ አይደለም፤ ሌላ በቅድምና የነበረ ሥጋ ነው የሚሉ መናፍቃን መወገዝ፤

መ/ በኒቅያ ጉባኤ በተረቀቀው ጸሎተ ሃይማኖት ላይ የተጨመረ፣ አምስት አንቀጽ ያለው የሃይማኖት ቀኖና መረቀቅ ነው:: ከዚህም ጋር የኒቅያውን ረቂቅ ምስጢሩን ሳይሆን፣ ንባቡን ለማስተካከል በዚህ ጉባኤ የገቡ አንዳንድ ቃላት አሉ::

መቅዶንዮስ ቍጥሩ ከመንፈቀ አርዮሳውያን ነው:: አርዮሳውያን ገንነው ቍስጥንጥንያን ባጥለቀለቁበት ሰዓት፣ እየተመላለሰ የቍስጥንጥንያን መንበር ይዟል (በ342-346፣ 351-360):: የሞተው በ364 ዓ.ም ነው::

ይኸው መናፍቅ፣ ከቅድስት ሥላሴ ሦስተኛው አካል መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው (ፍጡር ነው) ብሎ በቍስጥንጥንያና በአካባቢዋ መርዙን ባገሳ ጊዜ፣ በግሳቱ የተመረዙ አጽራረ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ መናፍቃን ቤተ ክርስቲያንን ሲያውኳት ኑረዋል::

ይህ የመቅዶንዮስ ክህደት በተሰማ ጊዜ፣ እንደ ተለመደው ቤተ ክርስቲያን የተቃውሞ ድምጿን አሰማች:: ያን ጊዜም የቍስጥንጥንያ ንጉሥ የነበረው ቴዎዶስዮስ ቀዳማዊ፣ ይህን የቤተ ክርስቲያን ችግር የሚፈታ ጉባኤ በቍስጥንጥንያ እንዲደረግ፣ ለቤተ ክርስቲያን አባቶች መልእክት አስተላለፈ:: በዚህ ምክንያት 150 ሊቃውንት ኤጲስቆጶሳት በቍስጥንጥንያ ተሰበሰቡ (በ381 ዓ.ም)፣ የዚህ ጉባኤ ሊቃነ መናብርት ብዙ ጊዜ ተለዋውጠዋል:: በመጀመሪያ የተሠየመው ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ (ነባቤ መለኮት) ነበር፤ እሱ ወዲያው ሊቀ መንበርነቱን ሲተው፣ ኔክታሪዎስ የተባለ መጥሮጶሊስ ተሠየመ፤ ኔክታሪዮስም እንዲሁ ሊቀ መንበርነቱን ተወ፤ በዚህ ጊዜ ጢሞቴዎስ (ዘአልቦ ጥሪት) የተባለው የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ ተሠየመ:: ግንቦት ወር 381 ዓ.ም የመቅዶንዮስ ጉዳይ ለጉባኤው ቀረበ፤ መንፈስ ቅዱስ ሕጹጽ ነው፤ ፍጡር ነው፤ ለማለቱ ግን ያቀረበው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንጭ አልነበረውም:: ጉባኤው በጥሞና ሁኖ ስለ መንፈስ ቅዱስ አምላክነት በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉትን ምስክሮች፣ በኢሳይያስ ምዕራፍ 6፣ «ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባኦት» እያሉ ሲያመሰግኑ የሰማቸው መላእክት «የአብ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን» አንድ አምላክነት፣ የአካልን ሦስትነት፣ የባሕርይን አንድነት መመስከራቸው መሆኑን ገልጧል:: ከዚህም ጋር ራሱ ጌታ በመጨረሻ ለሐዋርያት በሰጠው ትእዛዝ፣ «አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ» አንድ አምላክ ናቸው እንጂ፣ የሚበላለጡ አለመሆናቸውን ገልጦ ተናግሮአል::

ነገር ግን መቅዶንዮስ በአርዮስ ፈር የሚጓዝ ተረፈ አርዮሳዊ ስለሆነ፣ ከአርዮሳዊ አስተሳሰቡ ፍንክች አላለም:: ከዚህ በኋላ 150 ሊቃውንት እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ ሁነው መንፈስ ቅዱስን ሕጹጽ (ፍጡር) የሚል፣ የመቅዶንዮስን ትምህርት አውግዘው፣ የሠለስቱ ምእትን ትምህርተ ሃይማኖት አጽድቀዋል::

ከዚህም ሌላ፣ ይኸው ጉባኤ የአቡሊናርዮስን ትምህርት አውግዟል:: አቡሊናርዮስ (አፖሊናርዮስ፣ ከ310-490) በታናሹ እስያ በሎዶቅያ ተወልዶ ያደገ ሰው ነው፣ የትርጓሜው ስልት የእስክንድርያን ትምህርት ቤት ስልት ይከተል ስለነበር፣ የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ የሚያውቁ ሰዎች ከእስክንድርያ መናፍቃን ይቈጥሩታል:: አቡሊናርዮስ የፕላቶንን ፍልስፍና ወስዶ ሰውን ለማወቅ ለማሰብ የምታስችለው ነባቢት፣ ለባዊትና፣ ሕያዊት ነፍስ ከመለኮት ተከፍላ የመጣች ናት ብሎ ያምን ነበር:: ስለዚህም በምስጢረ ሥጋዌ አምላክ ሰው በሆነ ጊዜ፣ የተዋሐደው ሥጋን እንጂ ነፍስን አይደለም፤ ስለ ነፍስ፣ በነፍስ ፈንታ መለኮት ለሥጋ ነፍስ ሆነው፤ ሁለቱ ማለት ነፍስ መለኮት ለመዋሐድ አይችሉምና ብሏል:: «ሀየንተ ነፍስ ወልቡና ኮነ መለኮቱ» አቡሊናርዮስ ለዚህ አስተሳሰቡ አስረጅ እንዲሆነው ያቀረበው በዮሐንስ ወንጌል 1÷14 «ቃል ሥጋ ኮነ» የሚለውን ንባብ ነበር:: በሱ አስተሳሰብ ዮሐንስም መለኮት ሥጋን እንጂ ነፍስን አልተዋሐደም ያለ መስሎት ነበር:: ነገር ግን ዮሐንስ (ዮሐ 11÷33-38፣ 12÷27፣ 13÷21) በተከታታይ ጽሑፉ እንደሚያስረዳው ቃል ሥጋ ሆነ ማለቱ የእግዚአብሔር ቃል ነፍስንም ሥጋንም ተዋሐደ ማለቱ እንጂ ከፍሎ ተዋሐደ ከፍሎ ተወ ማለቱ አይደለም:: መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ሰው ለማለት ሥጋ ይላል:: ነቢዩ ኢዮኤልም እንደ ዮሐንስ አባባል ሰው ለማለት «ሥጋ» ብሏል:: ለምሳሌ ኢዮኤል 2÷28 «እሌኑ መንፈስየ ዲበ ኵሉ ዘሥጋ» በሥጋ ሁሉ ላይ ማለቱ እንጂ ነፍስ በሌለው ሥጋ ላይ ወይም በበድን ላይ ማለቱ አይደለም:: «ነፍስ» «ሥጋ» ብሎ ሰው ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ የተለመደ ነው (1ኛ ጢሞ 3÷17)::

የአቡሊናርዮስን አስተሳሰብ፣ በዘመኑ የነበሩ ሊቃውንት ይልቁንም ጎርጎርዮስ ዘእንዚናዙ ሰው የሚባለው ነፍስና ሥጋ ነው:: መለኮት ሥጋ ሁኖ ሰውን አዳነ ማለትም ነፍስንም ሥጋን ተዋሕዶ ነፍስንም ሥጋንም አዳነ ማለት ነው:: ሥጋ እንጂ ነፍስ አልነሣም፣ አልተዋሐደም ከተባለማ «ዘኢተነሥአ ኢድኅነ ወይም ኢያድኅኖ ለዘኢነሥአ» ቃለ እግዚአብሔር ወልድ ያልተዋሐደውን አላዳነውም:: የሰው ሥጋው (ቆዳው) እንጂ፣ ነፍሱ አልዳነም ማለት ይሆናል ብሎ መልሷል:: ምን ጊዜም የኦርቶዶክስ ሊቃውንት የአምላክን ሰው መሆን የሚተረጕሙት ከሰው መዳን ጋር አዛምደው ነው:: ከተዛነፈ ግን ሁሉም ቀረ ነው:: ይኸው የኦርቶዶክሳዊ ሊቅ ጎርጎርዮስ እንደ ጻፈው፣ ሥጋ በቅድምና ነበረ፤ ባሕርዩን አግዝፎ ታየ ብሎ ያስተማረም ይኸው አቡሊናርዮስ ነው:: ይህ ከግኖስቲኮች የተወረሰ የአቡሊናርዮስ አስተሳሰብ መጀመሪያ በ362 ዓ.ም በእስክንድርያ ሲኖዶስ ተወግዟል፤ ሁለተኛም በአንጾኪያ ሲኖዶስ 379 ዓ.ም ተወግዟል:: በመጨረሻም በዚህ በጉባኤ ቍስጥንጥንያ ተወግዟል:: ከዚህ በኋላ ግን እየጠፋ ሔዷል:: መለካውያን ግን ወደ ፊት እንደምናየው የአትናቴዎስንና የቄርሎስን አንድ ባሕርይ ትምህርት ከአቡሊናርዮስ የተወረሰ አድርገው ፈራ ተባ እያሉ ይናገራሉ:: ነገሩ ግን «ጨኸቱን ቀማችኝ» እንደተባለው ነው እንጂ፣ የአቡሊናርዮስን ትምህርት የሚመስል የራሳቸው ትምህርት ነው:: ይህንም ኋላ በቦታው እናመጣዋለን::

ይህ ጉባኤ የሠለስቱ ምእትን ትምህርተ ሃይማኖት አጽድቆ መናፍቃንን አውግዞ ከመለያየቱ በፊት፣ በጉባኤ ኒቅያ አንቀጸ ሃይማኖት ውስጥ ተጨማሪ (ሥርዋጽ) ቃላትና አምስት አንቀጾች ያሉት ተጨማሪ ጸሎተ ሃይማኖት አርቋል:: እንዲሁም ሰባት ቀኖናዎችን ሠርቷል:: ተጨማሪ ሆነው (ሥርዋጽ) የገቡት ቃላት የሚከተሉት ናቸው፤ «እመንፈስ ቅዱስ ወእማርያም ድንግል» (ወተሰቅለ በእንቲአነ በመዋዕለ ጲላጦስ ጳንጤናዊ» ሐመ ወሞተ ወተቀብረ» በከመ ጽሑፍ ውስተ መጻሕፍት ቅዱሳት» «ወነበረ በማየነ አብ» «በስብሐት» «ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ» እነዚህ ምንባባት በጉባኤ ኒቅያው አንቀጸ ሃይማኖት እንደ ማሟያ እየሆኑ የገቡ ናቸው:: ሌሎች ባለ አምስት ተራ ቍጥር ምንባባት ደግሞ «ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ» ብለው ሠለስቱ ምእት የጀመሩትን እነዚህኞቹ የተሰበሰቡበት ዋናው ምክንያት የመንፈስ ቅዱስ ነውና የሱን ማንነት በይበልጥ አብራርተውታል::

<u>የቍስጥንጥንያ አንቀጸ ሃይማኖት</u>

1. ወነአምን በመንፈስ ቅዱስ እግዚእ ማኅየዊ ዘሠረጸ እምአብ ንስግድ ሎቱ ወንሰብሖ ምስለ አብ ወወልድ ዘነበበ በነቢያት፤ (በጌታ በአዳኝ ከአብ በሠረጸ ከአብና ከወልድ ጋር በነቢያት በተናገረ በመንፈስ ቅዱስ እናምናለን እንሰገድለት እናመሰግነው)
2. ወነአምን በአሓቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኵሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት (በሁሉ ባለች በሐዋርያት ጉባኤ ባንዲት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን)፤
3. ወነአምን በአሐቲ ጥምቀት ለሥርየተ ኃጢአት፤ (ለኃጢአት ማስተሥረያ ባንዲት ጥምቀት እናምናለን)፤
4. ወንሴፎ ትንሣኤ ሙታን (የሙታን ትንሣኤን ተስፋ እናደርጋለን)::

ወሕይወተ ዘይመጽእ ለዓለመ ዓለም (የሚመጣውን ሕይወት እንጠባበቃለን ለዘለዓለሙ አሜን)::

ይህ ከዚህ በላይ ያየነው በጉባኤ ቍስጥንጥንያ የተረቀቀው አንቀጸ ሃይማኖት ከፊተኛው ጋር አንድ ሆኖ ዛሬ በሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያናችን ይሠራበታል::

በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ግን «ዘሠረጸ እምአብ» በሚለው «ፊሊኦክዌ» ወእም ወልድ ማለት ነው» ተጨምሮ፣ «ዘሠረጸ እም አብ ወእም ወልድ» ይላሉ:: ይህም የተጨመረው 1014 ዓ.ም በፓፓ በኔዲክቶስ ዕብሬት (ዘመን) ነው::